# <u>ሆያ ሆዬ ፖለቲካ</u>

**ይቅር ደሞዜ**

ፖለቲካ ሁሌም ጥርት ብሎ የሚገኝ ክስተት ወይም ሂደት አይደለምና የአማራ ወያኔ የአፍሪካ አሜሪካዊ ሪፑብሊካን እንደሚኖር ማዳም ራይስና በጋዜጣ ህወሓት እናቴ ናት ያለውን ወንድወሰን ከበደን ብቻ በመጥቀስ ማለፍ የሚቻል ነው:: ፖለቲካ እንደ ማንኛውም የሰው ልጅ ስራና ስምሪት ውስብስብ ነው:: ፖለቲካ ራሱ ሳይንስ ነው ተብሏል:: ከሆያ ሆዬ ጋር ግንኙነት የለውም::

ሁላችንም በሰው ፍጡርነታችን ሆነ በተወሰነ ህብረተሰብ ውስጥ ነዋሪ በመሆናችን ከፖለቲካ ልንርቅ አንችልም:: ፖለቲካ አንገባም፤ ፖለቲካ አልወድም ወዘተ ሲባል የሚሰማ ቢሆንም ከፖለቲካ ጭራሽ ሳይገናኝ የሚችል ሰው የለም:: ፖለቲካ በሀገር ደረጃ በሕዝብና መንግስት መሀል ያለውን ግንኙነትና ቅራኔ የሚገልፅ ሲሆን ሀገሮች መሀል ያለውንም ግንኙነት ይመለከታል:: የህብረተሰብን ዕድገት ግንዛቤ በሳይንሳዊና ትክክለኛ መንገድ የተረዳና የሚከተል ፖለቲካ እንዳለው ሁሉ የጥቂቶችን ጥቅም አስቀድሞ የህብረተሰቡ ቀና ዕድገት የሚጠይቀውን ሂደት ተፃር የሚሄድም ፖለቲካ አለ :: በዚህ መስክ የርዕዮት ጉዳይ ቦታና ክብደት ይዞ መገኘቱ ደግሞ የሚታይ ነው:: ፖለቲካ ዛሬና ነገ ህይወታችንን የሚወስንልንና የሚቃኝልን ነውና በቀላሉ ልናየው፤ ለቀቅ አርገን ልንይዘው የሚገባን ጉዳይ አይደለም:: በተለመደው አነጋገር ፖለቲካ የሞት ሽረት ጥያቄ ነው:: የቡሄ ሆያ ሆዬ አይደለም::

ይህ ሲባል ፖለቲካ የምርጦች ወይም ባለፈው ሰሞን በመጣው አነጋገር ደግሞ የሊሂቆች ብቻ ነው ተብሎ ሕዝብ ይገለል ማለት አይደለም:: ሕዝብ ፖለቲካ ማለትም ዕጣ ፈንታዬ ይመለከተኛል ብሎ ካልተነሳ የሀገር ሁኔታ ሊሻሻል እንደማይችል ይታወቃል:: በየካቲት 66 አብዮት ጭቁኑ ሕዝብ ለመብቱ አብሮና አምርሮም በመነሳቱ አፈናና እመቃ ቢደርስበትም ስርዓቱን ለመጣል ቻለ:: በዚያን ጊዜ የነበረው የድርጅታዊ አቅም ማለትም ፖለቲካዊ ብስለት ገና በመሆኑ የታጠቁ መኮንኖችና ወታደሮች ያላረገፉትን የስልጣን ሾላ ብቸኛ በዪ ሆነው ተገኙ:: ደርግ የተባለው ጭራቅ በሀገሪቷና በሕዝቧ ላይ ተጫነ :: መከራ ተከተለ :: በቀይ ሽብርም የተነሳ ፍርሀት ሰፍኖ ብዙዎች ፖለቲካ እንደ ኮረንቲ ብለው የወሰዱት አቋዋም በስልጣን የነበረውን ደርግ ረዳው:: ምክንያቱም በፖለቲካ አልገባም ማለት ራሱ ፖለቲካ ነውና ነው:: በፖለቲካ መግባትና መሳተፍ ያለበት ህዝብ እንደፈለጋችሁ ግዙን ብሎ አንገቱን ከደፋ በራሱ ላይ ካቴናውን አጠበቀ ማለት ነው::

ፍሬ የሚያስገኝ ፖለቲካን ለመከተል ከተፈለገ በቅድሚያ ፖለቲካ ግርግር አለመሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል:: እንዲያው በአሰኘኝ የሚያዝ አይደለም:: የሀገሪቷን ሁኔታ በጥልቅ መረዳት ይገባል:: ጠላትና ወዳጅ መታወቅና መለየት አለበት:: የትግል ታሪክ መጠናት ይገባዋል ማለትም ከራስ ሕዝብና ከሌሎችም ተመክሮ ስለ ትግል መማር ተገቢ ነው:: ከክፉም ከደጉም ለመማር ማለት ነው:: ለምሳሌ ከላፈው ምርጫ ሂደትና ውጤቱ ብዙ መማር ይቻላል:: ስህተቶችን በተለይ ላለመድገም:: የፈላስፋው ድንጋይ የተባለው የእውቀት ምንጭ በእጃችን የለምና ቅርሳችን ነው እውቀታችን ብለን የሀገራችንን ታሪክ፤ ባህልና የትግል ተመክሮ ማወቅ መቻል አለብን:: ያ ጀግና የተባለውና በፋሺስቶች ጎራዴ የተቀላው ትውልድ ለሀገሩና ለሕዝብ ዕፁብ ድንቅ ፍቅር ቢኖረውም የሀገሩንና የሕዝቡን ሁኔታ በተመለከተ ግን ግንዛቤው በሚያስፈልገው ደረጃ እንዳልነበር ያኔ የነበሩትና የተረፉት ራሳቸው የነገሩን እውነታ ነው:: ሆኖም ግን ለመማርና ለማወቅ የተንሰፈሰፈና የተዘጋጀ ቅን ትውልድ ነበረና በጊዜ ተምሮ ከሕዝብ ተዋህዶ ትግሉን ሊቀጥል ችሏል:: ቀጠለ ብንልም ደግሞ በየጊዜው በመሀሉ እንክርዳድ ሊያፍነው እየተነሳ መዋደቅ ነበረበት:: ነፍጥ አንግቦ ማን ሊደፍረኝ ብሎ ለተነሳ ወታደራዊ ቡድን እጅ የሰጡ ክፍሎች ሙልጭ እንደ ስብቆ እንጣጥ እንደ ፌቆ ብለው ሰበብና ምክንያት ደርድረው ከአራጁ ጋር ግብር ሊገቡ በመነሳታቸው-- ክህደት በመፈፀማቸው-- ያ ሁሉ ዕልቂት ሊደርስ ቻለ :: ባንዳ ተባሉ አንጃ፤ ተንበርክኮ ትግል አሉ እናቁም አድማ ሁሉም የትግልን ባቡር ከሀዲዱ አላቀው ወደ ገደል ከተዋል:: ዛሬም የሁኔታ ለውጥ በሌለበት ዳግም በምርጫ እንሳተፍ የሚለውን አቅዋም የሚያስተጋቡት ሆነ ከአረመኔው መለስ ጋር ለመተሻሸት በግልፅም

በስውርም፣ አንዴ በኦስሎ አንዴ በወያኔ ኤምባሲዎች የሚዶልቱት ሁሉ በዚህ የሚፈረጁ ናቸው::

ወያኔ የሚባለው ወሮበላ ቡድን ለስልጣን ከበቃ ጀምሮ በተለይ በሆያ ሆዬ ፖለቲካ የተጓዙ የሕዝብን ትግል በጣም ጎድተዋል። ስለ ወያኔ ተገቢውን ግንዛቤና መረጃ ሳይዙ ሆይ ሆይ ብለው የደገፉት ትግልን ጎዱ። እነ ዶክተር በየነ፣ አነጎች፣ አሰፋ ጫቦ፣ ወልደ አማኑኤል፣ መሸሻ ብሩ፣ ከበደ ደስታ፣ ክፍሉ ታደሰ ወዘተ ሁሉም ከዚህ መርዘኛ እባብ ቡድን እንቁላል እርግብ ትወለዳለች ብለው ሲሰለፉና ሲለፍፉ -- ወይም አንዳንዶቹ ለሆዳቸው ሲያድሩ-- ወያኔ ይውደም ብለው ተሰልፈው ህይወት የገበሩትን ተማሪዎች፣ ወያኔና ሻዕቢያ ጨፍጭፈዋቸው የመጡትን ሕዝብና ኢሕአፓዎች አፈር ቸለሱባቸው። ተደናግረው አደናገሩ። መለስን ደግፈው እጅ ያወጡት፣ የአርባ ጉጉና በደኖን ወንጀል የፈፀሙትና የደገፉትም ለራሳቸው መሰቀያ ገመዳቸውን ከማዘጋጀት ሌላ የሕዝብን ትግል ጎዱ። ፖለቲካው አልገባቸውም። የያያ ጉለሌና የሹመት ግርግር ፖለቲካቸውን በሆያ ሆዬ ወሰነው። የመለስ ዜናዊ ጠባብ ብሄረተኛ ቡድን ግን ሴራውን ጎንጉኖ ና ጊዜ ጠብቆ በላቸው። ይህ በቂ ተመክሮ ሆኖ ሳለ ፖለቲካው ዳግም ከምስጢረ ስላሴ በባሰ ምስጢር ሆኖባቸው ስህተት በስህተተ እየፈፀሙ ትግላችን መጎዳቱ ግልፅ ነው። በሽግግሩ ወቅት ከጀግናው ፕሮፌሰር አስራት በስተቀር ሌሎች የእነ መለስን ውሳኔ ደግፈው በመቆም ለግንጠላውም ለሌላውም ወንጀል ወደዱም አልወደዱም ተባባሪ ሆነዋል።

እየተገዙ መታገል በሚል፣ የኤኮኖሚ ትግል ይቅደም በሚል፣ ፖለቲካውን አደፍርሰው ለገዢው ክፍል መገዛትንና ጠባይ አሳምሮ ልምምጥ ማንገስን የሰበኩ ክፍሎች ዛሬም ቢሆን የውድቀት ፖለቲካን፣ የውርደት ፖለቲካን፣ የፍርሀት ፖለቲካን ያስቀደሙ ሆነው በመገኘት ያ ሁሉ ፍጅት ተካሂዶ ያገኘነውን ተመክሮ ወደ ጎን በመጣል በመጪው ምርጫ እንሳተፋለን የሚል አቀዋም ይዘዋል። ይህ የእነሱ ፖለቲካ ብልህነት መስሎ ባርነትን አንጋሽ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። በዚህም በዚያም ግን ለሆያ ሆዬ ፖለቲካ ለመራቅ ከፈለግን የኢትዮጵያ ፖለቲካ በአብዛኛው መልኩ የኢትዮጵያ መሆኑን መገንዘብ ይገባናል። ሀገራችን በዓለም ውስጥ እንደመኖሯና የሀገሮች የርስ በርስ ትስስር ( መሰረቱ የተዛባ ቢሆንም) ደግሞ የጠበቀ በመሆኑ የዓለም ፖለቲካ በኢትዮጵያ ላይ ጫና ያደርጋል። ቢሆንም፣ የሀገራችን ፖለቲካ የራሱ ማህተምና ይዘት የታወቀ በመሆኑ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ገፅታና ዝንባሌ ማወቅ ተገቢ ነው። በአሜሪካ የሲኒማ ተዋንያን ለፖለቲካ ስልጣን በቅተዋልና በኢትዮጵያም በደፈናው ገንዘብ ያለው ወይም በሩጫ ዝነኛ የሆነ ፖለቲካውን ይቃኘው ብሎ መተዉ ስህተት ነው። በአሜሪካ ሁለት ፓርቲ ብቻ ገኖ አለና ኢትዮጵያ ከሁለት ሶሶት ፓርቲ በላይ አያስፈልጋትም ብሎ ኢዴሞክራሲያዊ አቀዋም መያዝም ስህተት ነው። ኢትዮጵያ የራሷ ባህል፣ የፖለቲካ ትግልና ሰልፍ እንዲሁም ታሪክም ያላት በመሆኗ ፖለቲካዋ በዚህና ባልዋት መሰረታዊ ችግሮችና ሊቀርቡ በሚመረጡ መፍትሄዎች የሚወሰን ይሆናል።

ከ 97 ኡ ምርጫ በፊትና በህዋላም ሆያ ሆዬ ፖለቲካ ሰፍኖ ትግሉ መጎዳቱ የታየ ነው። የዚህ የግርግርና ቀደም ሞቅ ሞቅ ይሉት የነበረው ፖለቲካ ዋናው ምሳሌ ደግሞ ዛሬ ክህደቱ ያኔ ደግሞ 27 ወር ሳይታሰር ማንዴላ የተባለው ልደቱ አያሌው ነበር።ሌሎችም አልጠፉም። ክህደቱ ግን የራሱ ተልዕኮ (ማለትም ወያኔ የሰጠው) ቢኖረውም በንግግሩና ግራና ቀኙን ንክሻው የሆያ ሆዬን ፖለቲካ አንፀባርቋል። አለሁ አለሁ ብሎ ወዲያውም ተኖ ከመለስ ፓርላማ ተሸጉጦ በህዝብ ተወግዟል። የመለስ ዜናዊን መንግስት ጠባይ በተመለከተ ራሱ ትክክለኛ ግምገማ አልነበረም። እነ መለስና በረከት በምርጫ ተሸንፈው ስልጣን በሰላም ሲለቁ ሁሉ ይታሰብ ነበረ ። የሕዝብ መነሳሳትና የለውጥ ነፋስ መንፈሱ ብዙዎችን በሚያሰክር ሁኔታ ከቶ ነገ ምን ይመጣልን ማየት አቃተ ። አደብ ግዙ ብለው ያሳሳቡትን ሆ ያ ሆዬው አላሰማ አለ ። ከአሜሪካን ባለስልጣኗ ጋር ሆነው የሕዝብን አድማ ያፈረሱት እነ በየነ ጴጥሮስና ብርሃኑ ነጋ የዚሁ ሰለባ ነበሩ ማለት ይቻላል። ሰውየው በእስር ቤት እያሉ በአሉታዊ ብዙ መተቸት አግባብ ስለሌለው ብንተወውም ከዶክተር ብርሃኑ ነጋ መፅሀፍ ንባብ የሚቀሰመው አንደኛው ጠቃሚ ትምህርት ምንኛ ያኔ ሆይ ሆይ ይሉ የነበሩት የሀገራቸውን ፖለቲካ (ከእነ መለስ ማንነት እስከ ድርጅት አስፈላጊነት ወዘተ) በጥልቀት ማወቅ እንደተሳናቸው ነው። አጋርና ባላንጣም ስላልተለየ ለሕዝብ ቆመናል ያሉ ድርጅቶች በመተባበር ፈንታ በመጥፎ መፎካከርን መርጠው ለመለስ ጠቀሙ። ዛሬም ቢሆን በዚህ መስክ የተለየ አይታይም።

ፍርሀት፣ ክህደት፣ ሆያ ሆዬ-- ሁሉም ፖለቲካን ጠጋ ሲሉ የጠራውን ያደፈርሳሉ፡፡ ትግልን ይጎዳሉ፡፡ ለዚህም ነው የሀገራችንን ፖለቲካ ጠባይና መልክ ለማወቅ በመጣር ለመሰረታዊ የሀገራችንን ችግሮችና ቀውሶች በበሰለ ፖለቲካ መፍትሄ ለመስጠት መጣር መጣጣር ያለብን፡፡